የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አንደኛ አመት ቁጥር ፳፱
አዲስ አበባ ሰኔ ፱ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ/ም

1st year No. 29
ADDIS ABABA 18 February 2012

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፯ ዓ.ም
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ
አስተዳደርና አመራርና አዋጅ....................................ገጽ፩፻፷፰


Contents


Proclamation No. 10/2003
"A proclamation to Provide for the Addis Ababa
City Government Health Services Delivery Administration
and Management proclamation…………….page 168


## አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፯ ዓ.ም
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ
## አስተዳደርና አመራር አዋጅ

በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የጤና ተቋሞች አንድ ወጥ በሆነ የአሠራር፣ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት እንዲመራ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፤

የአዲስ አበባ ከተማ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃውን የጠበቀ እና በሥርዓት የሚመራ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

በመከላከል ላይ የተመሠረተውን የጤና አገልግሎት በሥልጠናና በሕክምና አገልግሎት እንዲደገፍ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በከተማ ውስጥ የጤና ተቋሞች ስለነባርና አዲስ ስለሚከሰቱ በሽታዎች እና የእነዚህም ሥርጭት ስላስከተለው ውጤት ከተማ አቀፍ የመረጃ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ በመታመኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞችን አደረጃጀትና የሥራ አመራር ማሻሻል፣ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት እንዲሁም መንግሥታዊ ካልሆኑ የጤና ተቋሞች ጋር ያላቸው ግንኙነት የሠመረ እንዲሆን ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስትዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬ (፩) (ረ) እና ፷፮ (፪) መሠረት የከተማው ጊዜያዊ አስተዳደር ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ፣ አስተዳደርና አመራር አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፭ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION No. 10/2003
## A PROCALAMTION TO PROVIDE FOR THE Addis Ababa CITY GOVERNMENT HEALTH SERVICE DELVERY ADMINSTRATION AND MANAGEMENT

WHEREAS, it has become necessary to operate health institution at different levels under uniform procedures control and follow up mechanisms፤

WHEREAS, it is necessary to ensure the provision of health services in Addis Ababa City Government have certain standards and systems;

WHEREAS, it is essential to support the promotive and preventive health activates with training and health service;

WHEREAS, it is believed that to make possible the existence of a city wide information base concerning existing and new outbreak of diseases and the magnitude of the problem resulting from their spread in a coordinated manner;

WHEREAS, it has become necessary to improve the structure and management of public health institutions, to facilitate the means by which these institutions obtain additional resources and create condition that will make possible smooth and functioning relationships between public and private health institutions;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 14(1) (F) and 66(2) of the revised charter of the Addis Ababa City Government Proclamation No. 311/2003, the provisional Government of the City proclaimed this as follows:

### PART ONE
### GENERAL

**1. Short Title**

This percolation may be cited as the "Addis Ababa City Government Health Service delivery administration and management proclamation No.10/2003."


ያንዱ ዋጋ 17.00
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

፪. **ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ

፩. “ከተማ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው ፣

፪ “የጤና አገልግሎት” ማለት የበሽታ መከላከል, ቁጥጥርን፣ የተላለፊ በሽታዎች ቅኝትን፣ የአካል የላብራቶሪ ፣ የራጅና ሌሎች ጤና ነክ ምርመራዎች የፈውስ ሕክምና የጤና አጠባበቅ ትምህርቶች ማሰራጨትና የኅብረተሰቡን የባህርይ ለውጥ መፈተሸና መገምገምና ያጠቃልላል፤

፫. “የነፃ ሕክምና” ማለት ወደፊት በከተማ መስተዳደሩ ካብኔ አካል በሚወሰነው ደንብ መሠረት ወጪው አግባብ ባለው ለሌላቸው የመንግሥት ወይም ሌላ ሶስተኛ ወገን ተሸፍኖ የመክፈል አቅም ዜጎች በነፃ የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ነው፤

፬. “ክፍያ የማይጠየቅበት የጤና አገልግሎት” ማለት የኅበረተሰቡን የጤና አጠባበቅ ጉልህ ጠቀሜታ ያላቸውን የጤና አገልግሎት ከመስጠት ጋር በተያያዘ ለሁሉም የኅበረተሰብ ክፍል ያለክፍያ የሚሰጥ አገልግሎት ነው፤

፭. “የጤና ተቋም” ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚተዳደር ሆስፒታል ፣ ጤና ጣቢያ ጤና ኬላና የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ማሰራጫ ዩኒት ነው፤

፮. “ካቢኔ ማለት” የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ነው፤

፯. “ገቢ”ማለት የጤና ድርጅቶች ከሚሰጧቸው ማናቸውም የጤና አገልግሎቶች የመድኃኒት፣ ሽያጭ እና ከሌሎች አገልግሎቶች እና ዕቃዎች ሽያጭ የሚያገኙት ገቢ እንዲሁም በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ የሚቀበሉት ዕርዳታ ነው፤

፰. “ሶስተኛ ወገን” ማለት የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን ወጪ / በኢንሹራንስ ወይንም በሌላ መልክ የሚሸፍን የግል ወይም የመንግሥት ድርጅት ማለት ነው፤

፱. “የግል የጤና ድርጅት” ማለት በመንግሥት የሚወጡ ሕጋዊ መሥፈርቶችን በሟሟላት በግል ባለሃብቶች ኢንቨስትመንት የሚቋቋም የጤና ድርጅት ማለት ነው፣

፲. “ቢሮ” እና “የቢሮ ኃላፊ” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮ እና የጤና ቢሮ ኃላፊ ነው፤

፲፩. “የግል ሕክምና መስጫ ክፍል” ማለት ከሆስፒታሎች የመደበኛ የሕክምና መስጫ ክፍል ውጪ የሆስፒታሉ አንድ ክፍል ሆኖ የሚቋቋም ለተመላላሽ ወይም ተኝተው ለሚታሙ ታካሚዎች የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ክፍል ነው፤

፲፪. “የቤተሰብ ገቢ” ማለት ቤተሰቡ ከማንኛውም እንቅስቃሴው በዓመት ወይም በወር የሚያገኘው በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ የሚገኝ ገቢ ማለት ነው፤

፲፫. “ወጪን የሚሸፍን አካል” ማለት የመክፈል አቅም ለሌላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚወጣውን የጤና ወጪ በጀት ይዞ የሚሸፍን አካል ማለት ነው፤

፲፬. “የግል ሴክተር” ማለት በጤና ዘርፍ ከመንግሥት መዋቅር ውጭ በግሉና በመንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚደራጁና የሚተዳደሩትን የሚያጠቃልል ነው፤

፲፭. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. **የጤና አገልግሎት አሠጣጥ መርህ**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች የጤና አገልግሎት የሚሰጡት በካቢኔው የሚወሰነውን ክፍያ በማስከፈል ይሆናል ፡፡

2. Definitions

In this proclamation

1. “City” Means the Addis Ababa City;
2. “Health Service” Means prevention and control of diseases, monitoring of contagious diseases, physical, laboratory, x-ray and other health examinations, curative treatment , the dissemination of health information and education as well as monitoring and evaluation of behavioral change in the society;
3. “Waiver” means a health service delivered in free of charge whose costs are covered by appropriate public body or by other third party decided by the future regulations of the city cabinet and provided to those persons who cannot afford payment;
4. “Exempted Service” means health service provided in freely to all community members irrespective of level of income to improve the utilization of health services that have externalities to the general public and often reflects market failures;
5. “Health institution” means hospitals health centers health posts, and health extension package dissemination unit, under the administration of the city Government;
6. “Cabinet” means the Addis Ababa City Government Cabinet;
7. “Revenue” means all revenue accruing to health institutions from health services they render sales of drug and other services and sales of goods as well as donations they obtain in cash or in kind ;
8. “Third party” means public or private organization which finances expenses of beneficiaries of medical services by insurance or other schemes;
9. “Private Health Institution” means a health institution established by private investors and that meets the legal requirements set by the Government;
10. “Bureau”” Bureau Head” means the Addis Ababa City Government Health Bureau and Head of Health Bureau respectively;
11. “Private wing” means a unit established whithn the hospital operating as the general part of a hospital outside the premises reserved for and out patients;
12. “Household Income” means the monthly or annual income earned in cash or in kind by a household from any activity;
13. “Body financing costs” means any body which by appropriation budget, covers the medical costs of patients who cannot afford to pay;
14. “Private sector” means that health services organized and managed by private and non-governmental organization;
15. “Person” means a natural or juridical person.

1. **Principles of Medical Service**

1. Health institutions of the city shall render medical service upon payment of the fees determined by the city cabinet.

፪. ከዚህ በላይ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ሰው የሚከፍለው በማጣቱ ምክንያት የጤና አገልግሎት ከማግኘት አይከለከልም፡፡

፫. በካቢኔው በሚወጣው ደንብ መሠት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የሚሰጡት የነፃ የሕክምና ማስረጃ በቂ ሆኖ ማንኛውም ሰው ነፃ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፡፡

፬.ፈቃድ ስለማግኘት

ማንኛውም የጤና አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የሚሰራ ሰው ከቢሮው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሳያገኝ ሥራ መጀመር አይችልም፡፡

፭. መድኃኒት

ማንኛውም ከመድኃኒት ጋር የተያያዙ ሥራዎች ማስመጣት ማምረት ማከፋፈል መሸጥ እና ለታካሚዎች ማዘዝ በመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፮/፲፱፻፺፩ ዓ.ም በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

የጤና አገልግሎት አስተዳደር

፮. የጤ ና አልግሎት አስተዳደር የስልጣን አካላት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አስተዳደር የሥልጣንና አካላት

፩. የጤና ቢሮ፣

፪. የመማክርት ጉባዔ፣

፫. የሆስፖታሎች የሥራ አመራር ቦርድ፣

፬. የሆስፒታሎች አመራር፣ እና

፭. የመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ተቋማት አመራር ናቸው፡፡

፯. የጤና ቢሮ ኃላፊ ስልጣን

በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች ከተሰጠው ስልጣን በተጨማሪ የጤና ቢሮ

ኃላፊው የሚከተለው ስልጣን ይኖረዋል፣

፩ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ሊኖራቸው የሚገባውን የሰው ኃይል ብዛት፣ ብቃትና ስብጥር፣ የሕንፃ የሕክምና መሣሪያዎች እና የመገልገያዎች ደረጃ ይወስናል፣

፪ ለግል የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ፈቃድ ማረጋገጫ ይሰጣል፣

፫ የከተማው አስተዳደር የጤና ተቅሞች በሚያቀርቡት ሃሣብ መሠት ለሚሰጡት የጤና አገልግሎት ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ የተቋሞቹን ወጪ እና የሕዝቡን የመክፈል አቅም ከግምት ማስገባቱን በማረጋገጥ አስፈላጊ ከሆነ በማሻሻል ከአስተያየት ጋር ለካቢኔው አቅርቦ ያስወስናል፣

፬ የከተማው አስተዳደር የጤና ተቋሞች የሰው ኃይል ብቃት የአሠራር ሥርዓት እና ድርጅታዊ አቅም እንዲጠናከር ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፣

፭ የጤና ድርጅቶችን ደረጃ መለየት የሚያስችል የመመዘኛ መመሪያ ያወጣል፣ በዚህም መሠት ለጤና አገልግሎት መስጣ ተቋሞች ደረጃ ይሰጣል፣

፮. በከተማው ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት የግብረሰናይና አትራፊ የሆኑ የግል ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ደረጃውን የጠበቀ አልግሎት የሚሰጡ ስለመሆኑ ይቆጣጠራል፣

፯. የጤና አገልግሎትን ለማስፋፋትና ጥራቱንም ለማሻሻል የወጡ ልዩ ልዩ መሥፈርቶች መመሪያዎችና ደንቦች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣

2. Notwithstanding the provisions of sub article 1 of this article , no person shall be denied of health services upon reason of not being able to pay .
3. A person who produces waiver certificate issued by bodies authorized by the City Council shall be entitled to health services free of charge
4. License

No person shall provide health services without getting professional competence confirmation certificate from the bureau.

5. Drugs

Activities related with drugs, such as importation, manufacture, distributions, sale and prescription, shall only be carried out in accordance with drug administration and control proclamation No. 176/1999

**Part two**

**Health Service Administration**

6. Organs of health service administration

Organs of the Addis Ababa City Government health service administration are

1. Health Bureau
2. Advisory Council ;
3. Management Board of Hospitals:
4. Management of Hospitals; and
5. Management of Primary health care units.

7. Powers of the head of health bureau

In addition to the powers vested upon the bureau head in other provisions of this proclamation, the bureau head shall have the power to:

1. determine the standards for the number, qualification and composition of manpower , buildings, medical equipment and Instruments for different levels of health institutions;
2. issue license to private health institutions;
3. upon the recommendation of health institutions and taking into consideration the cost of health institution and the ability to pay of the residents, the bureau shall propose to and get endorsement from the city cabinet the fees and charges payable for health services.
4. assist health institutions to improve the efficiency of their manpower, develop their operational systems and institutional capacity;
5. develop criteria to classify health institutions into different levels , apply same to classify them;
6. supervise health institutions run by the government charitable organizations and private profile making organizations. In the city to ensure that these institution are rendering medical service consistent with the approved standard;
7. Follow up and control the proper implementation of various criteria, directives and regulations issued tor the expansion and improvement of health service;

፰. **የመማክርት ጉባዔ**

፩. በከተማው የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ መሠረት በማድረግ የጤና አገልግሎቱ ሽፋንና ጥራት በሚሻሻልበት የጤና ዕቅዶች ላይና በዓመታዊ እቅድ አፈፃፀም ላይ በመምከር አስተያየት የሚሰጥ የመማክርት ጉባኤ ተቋቁሟል ፡፡
፪. የምክር ቤቱ አባላት ብዛትና ስብጥር እንዲሁም ስልጣንና ተግባር ጤና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
፫. የመማክርት ጉባዔው አባላት በቢሮው ኃላፊ ይሰየማሉ
፬. የቢሮው ኃላፊ የመማክርት ጉባዔው ሥራ የሚመራበትን ሁኔታ የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

፱ የሆስፒታሎች አቋም

፩ በከተማው አስተዳደር ሥር ያለ እያንዳንዱ ሆስፒታል በሥራ አመራር ቦርድ የሚመራ ሆኖ የሕግ ሰውነት ይኖረዋል፡፡
፪ እያንዳንዱ ሆስፒታል የንብረት ባለቤት መሆን መክሰስና መከሰስ በስሙ ውል የመፈፀም ፣ የባንክ ሂሣብ መክፈት እና ሀብቱን በልማት ላይ ማዋል ይችላል ፡፡
፫ የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ እና የሆስፒታሎች ሥራ አስኪያጅ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት እንዲሁም ተጠያቂነት ወደፊት በካቢኔው በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

**፲ የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ መቋቋም**

፩ በከተማው አስተዳደር ሥር ባለ በማንኛውም ሆስፒታል በበላይነት የሚያስተዳድር ተጠሪነቱ ለጤና ቢሮው የሆነ የሥራ አመራር ቦርድ ይቋቋማል፡፡
፪ የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ እንዲሁኔታው ቢያንስ አምስት ቢበዛ ሰባት አባላት ይኖሩታል፡፡ አሰያየሙም የጾታ ተዋጽኦን ባገናዘበ መልኩ ይሆናል፡፡
፫ የቦርድ ሰብሳቢ በከተማው ከንቲባ ይሰየማል፡፡
፬ የሆስፒታሉ ዋና ሥራ አስክያጅ የቦርዱ አባልና ፀሐፊ የሠራተኞች ተወካይ ደግሞ የቦርዱ አባል ይሆናል፡፡
፭ የቦርዱ አባላት ለሚሰጡት አልገልግሎት አግባብ ያለውን የመንግሥት መመሪያ በመከተል በከተማው ምክር ቤት የሚወሰን አበል ይከፈላቸዋል፡፡

፲፩ የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

የሥራ አመራር ቦርዱ

፩ የሆስፒታሉን አጠቃላይ የሥራ አንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፤
፪ የሆስፒታሉን የአጭር፣የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅድ መርምሮ ያፀድቃል፤
፫ የሆስፒታል ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ ያፀድቃል፣ የበጀት ረቂቅ መርምሮ ለቢሮው ኃላፊ ያቀርባል፤
፬ የሆስፒታሉን ወርሃዊ ፣ የሩብ ፣ የግማሽ እና ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ ሪፓርት መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል፤
፭ የሆስፒታሉ የገቢ ምንጮች የሚዳብሩበትን መንገድ ይቀይሳል.በተግባር ላይ መዋላቸውን እና ገቢ መደረጋቸውንም ይቆጣጠራል፤
፮ የሆስፒታሉን የሥራ እንቅስቃሴ የሚያሻሽል የውስጥ ደንብ ያጸድቃል፡

8. Issue directives for the implementation of this proclamation.

8. **Advisory council**

1. There shall be established an advisory council to assist efforts to improve the coverage and quality of health services in the city.
2. The number and composition of members as well as powers and duties of the advisory council shall be determined by a directive council shall be determined by a directive issued by the bureau.
3. Members of the advisory council shall be designated by the head of the bureau.
4. The head of the bureau shall issue directive to determine the condition in which the advisory council carries out its duties.

9**. Personality**.

1. Each hospital under the city Government shall be administered by a management board having its own legal personality.
2. Each hospital has the right to own property, sue and be sued on its own name, enter into contract, operate bank account and invest its resources in development projects.
3. Powers. Functions and accountability of the management board and general manager of the hospital shall be determined by a regulations issued by the cabinet.

10. **Establishment of Management Board in Hospitals**

1. There shall be established in every hospital under the city government a management board, accountable to the bureau that will administer the hospital.
2. The management board of the hospitals shall have a minimum number of five and a maximum number of seven members the nomination shall take into account gender balance.
3. The chairperson of the board shall be designated by the mayor.
4. The general manager of the hospital shall be member and secretary of the board and representative of the staff shall be a member of the board.
5. Members of the board shall be paid allowance for the service they render that the amount is to be determined by the city council in accordance with the relevant directive of the government.

11. **Duties and Responsibilities of the management Board of Hospitals**

The management board shall:

1. oversee and supervise the activists of the hospital ;
2. Examine and approve short, medium and long term plans of the hospital;
3. approve the annual work plan of the hospital ; examine the budget proposal and submit it to the head of the bureau;
4. examine and decide upon monthly, quarterly, semiannual and annual reports of the hospital;
5. devise mechanisms and strategies to raise the revenue of the hospital and monitor the implementation of same ensure that revenues are properly collected and timely deposited;
6. approve internal regulation that guide the proper carrying out of the activities of the hospital.

፯. የሆስፒታሉ ዋና ስራ አስኪያጅ ይቀጥራል፣ የመምሪያ አገልግሎት ኃላፊዎችን ቅጥርና እድገት ያፀድቃል፣

፰ የጤናው ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በውል ለሶስተኛ ወገኖች ሊሰጡ የሚችሉትን ከሕክምና ውጪ ያሉ አገልግሎቶች ይወስናል፣

፱ በኃላፊነት መደብ ለሚመደቡ የወንበር አበል ይወስና፣

፲ የሆስፒታሉ የስራ እንቅስቃሴዎችን ግልጽነት፣ የሙያ ሥነ-ምግባር እና ተጠያቂነት በሰፈነበት ሁኔታ እንዲከናወኑ ያደርጋል፣

፲፩ ቢሮው የሚያወጣቸው መመሪያዎች በሆስፒታሉ ውስጥ በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣

፲፪ በሆስፒታሉ ዋና ስራ አስኪያጅ የሚቀርቡለትን ሌሎች ጉዳዮች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**፲፪ የሆስፒታል ሥራ-አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር**

፩ የሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ የሆስፒታሉ ዋና ስራ አስፈጻሚ ሆኖ ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የሆስፒታሉን ሥራዎችን ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰው ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ስራ አስኪያጁ፣

ሀ) የክልሉን ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሰረታዊ መርሆዎች ተከትሎ ጊዚያዊ አስተዳደሩ በሚያጸድቀው መመሪያ መሰረት የሆስፒታሎችን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

ለ) የሆስፒታሉን የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣

ሐ) የሆስፒታሉን የሥራ ክንውን የሂሣብ ሪፓርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣

መ) ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት የሆስፒታሉ ኃላፊዎች በሠራተኞች አስተዳደርና ደንብ መሠረት አወዳድሮ በመምረጥ ለቦርድ አቅርቦ ያስጸድቃል እና

ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ሆስፒታል ይወክላል፡፡

፫. ዋና ሥራ አስኪያጁ ለሆስፒታሉ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሆስፒታሉ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

**፲፫. የቦርዱ ተጠያቂነት**

፩ የቦርዱ ሰብሳቢ እና አባላት ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፲ የተሰጣቸውን ተግባር በጥንቃቄ መፈጸም አለባቸው፡፡

፪ ሰብሳቢውን አባላቱ ተግባራቸውን በአግባቡ ባለመፈጸማቸው ምክንያት በሆስፒታሉ ላይ ለሚደርሰው ጉዳይ በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

፫ በአብላጫ ድምጽ በሚሰጠው ውሣኔ ለሚደርሰው ጉዳይ የተለየ ድምጽ ያለው አባል ተጠያቂ አይሆንም፡፡

7. employ the general manager approve the employment and promotion of heads of the departments and services of the hospital ;
8. in accordance with the directive issued by the b ureau determine non-clinical services that may be given to third parties by contract;
9. deremine the responsibility allowance payable to persons assigned to posts of responsibilities;
10. ensure that the activities of the hospital are carried out with transparency, professional ethics and accountability;
11. ensure that the directives issued by the bureau are properly implemented in the hospital;
12. examine and decide upon other matters that are submitted to it by the General Manager.

**12. POWERS AND DUTIES OF THE GENERAL MANAGER**

1. The general manager as the chief executive of the hospital shall direct and manage the activites of the hospital in accordance with general instructions given to him by the management board.
2. Without prejudice to the generality stated in sub article 1 of this Articles, the General Manager shall ;
   (a) employ, administer and dismiss employees of the hospital in accordance with the directives approved by the provisional government in conformity with the basic principles of the city's civil service law.
   (b) prepare and submit to the management board the budget and work program of the hospital; and implement same upon approval;
   (c) prepare and submit to the management board the operation and financial reports of the hospital;
   (d) select by competition the heads of the departments accountable to him and submit to the board for approval and
   (e) represent the hospital in all its dealings wigh third parties.
3. The general manager may delegate part of his powers and duties to the officials and employees of the hospital to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the hospital.

**13. Accountability of the Board**

1. The chairman and members of the board shall execute their duties vested in under article 10 above with due care.
2. The chairman and members of the board shall jointly and severally be liable for damages caused due to the failure to execute their duties with due care.
3. Dissenting members may not be responsible for any damage caused as a result of the decision passed by majority vote.

## ክፍል ሶስት

### የጤና አገልግሎቶች የሚሰጥበት አኳኋን

፲፬. የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት

፩ የከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት በሶስት ደጃዎች የሚከፈሉ ሲሆኑ እነዚህም ፣

ሀ) ሆስፒታል፣

ለ) የጤና ጣቢያ እና

ሐ) የጤና ኬላ ናቸው፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተዘረዘሩት ደረጃዎች በሚገኙ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ውስጥ የሚያገለግለው የሰው ኃይል፣ መገልገያዎች እና የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ በቢሮው ይወሰናል፡፡

፲፭ የሙያ ሥነ ምግባር

ቢሮው የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የጤና ተቋማት እና በእነዚህ የጤና ተቅማት ውስጥ የሚሠሩ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ሊከተሉት የሚገባውን የሙያ ሥነ ምግባር የሚመራ ደንብ አዘጋጅቶ በካቢኔው አፀድቆ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

፲፮ የሕሙማን አላላክና አቀባበል ሥርዓት

ሕሙማን አስፈላጊውን የጤና አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ከአንድ የጤና ተቋም ወደሌላ የሚላኩበት ሥርዓት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፲፯. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሎች ስለማቋቋም

፩. ሆስፒታሎች የሆስፒታሉ አንድ ክፍል ሆኖ የሚሠራ የግል ሕክምና መስጫ ክፍል ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡

፪. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሎች አሠራር ፣ አመራርና አስተዳደርን የሚወስን ዝርዝር መመሪያ በቢሮው ይወጣል፡፡

## ክፍል አራት

### የነፃ ሕክምና አሰጣጥ እና ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች

፲፰. ስለ ነፃ የሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች

፩. የመክፈል አቅም የሌላቸው ስለመሆኑ የነፃ ሕክምና ማስረጃ የሚያቀርቡ ዜጎች በከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ነፃ የሕክምና አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

፪. የነፃ ሕክምና የሚሰጥበት ሥርዓት ማለትም ተጠቃሚዎች የሚለዩበት ማስረጃ በማን እና እንዴት እንደሚሰጥ፡ ወጪውም በማንና እንዴት እንደሚሸፈን ወደፊት በአዲስ አበባ አስተዳደር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፲፱. በክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች

፩. የከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የጤና አገልግሎቶች ያለክፍያ ይሰጣሉ፡

ሀ) የሳንባ ነቀርሳ በሽታ፣ አክታ ምርመራ፣ ክትትልና የመድኃኒት አቅርቦት፡

ለ) የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት፡

ሐ) የቅድመ እና ድኅረ የወሊድ አገልግሎት፣

መ) በመሠረታዊ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚሰጥ የማዋለድ አገልግሎት

ሠ) ፀረ ስድስት የሕፃናት በሽታ ክትባት፣

ረ) ከእናት ወደ ጽንሱ HIV/AIDS እንዳይተላለፍ መከላከል፣

ሰ) ሥጋ ደዌ፡

ሸ) ወረርሽኝ፡ እና

## PART THREE

The Manner in which Medical Services may be provided

**14.** Health delivery institution.

1. There shall be three levels of healthe institutions in the city these are;
   (a) hospital ;
   (b) health center and
   (c) health post
2. The bureau shall determine qualification of man power standard of equipment and service provision in the health institutions under sub-article 1 of this article.

**15.** Code of conduct

The bureau shall develop code of conduct according to which public and private health institutions and medical and non- medical staff serving in such institutions must comply when performing their duties and cause same to be timplemented after obtaining approval from the cabinet.

**16.** Referral system

The referral system according to which patients may be provided proper medical care shall be determined by a directive to be issued by the bureau.

**17.** Establishemt of the private wings.

1. Hospitals may establish a private wing that operates as part of the general hospital.
2. The bureau shall issue a detailed directive to determined, the operation and management of the private wing.

## Part four

Waiver scheme and exempted health service

**18.** Waiver scheme

1. Citizens who can produce evidence ascertaining the fact that they cannot afford to pay for health services are entiled to waiver scheme.
2. The manner in which beneficiaries are identified, how and by whom should certivficates of waiver are to be issued and how and by whom should the coas be reimbursed to facilities shall be determined by the regulations to be issued by city government council.

**19.** Exempted Health Services

1. The city government health service delivery institutions may render health service in free of charge in the following categories;
   (a) Diagnosis , following up and supply of medicaments for tuberculosis;
   (b) Family planning services;
   (c) Pre and post natal services;
   (d) Delivery service in basic health service institutions;
   (e) Expanded programme of immunization for children under five
   (f) Prevention of HIV/ADIS transfer from mother to child;
   (g) Leprosy;
   (h) Epidemic; and

ቀ) ወጪያቸው በመንግሥት የሚሸፈን ሆኖ ወደፊት ያለ ክፍያ እንዲሰጡ የሚወሰኑ ሌሎች የጤና አገልግሎቶች፡፡

፪. ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች የሚሰጥ የጤና ተቋም የዚህ ዓይነቶቹን አገልግሎቶች የሚያሳይ መረጃ ለይቶ በመያዝ ለቢሮው ኃላፊ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት
## የከተማው አስተዳደር ሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች ፋይናንስ

፳. የሆስፒታሎች /ጤና ጣቢያዎች የፋይናንስ ምንጭ

፩ በከተማው አስተዳደር በጥቅል የሚመደብ በጀት፣
፪ ከሚሰጡት የጤና አገልግሎት የሚያገኙት ገቢ እና
፫ ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በዓይነት በጥሬ ገንዘብ ከሚቀበለው ዕርዳታ ይሆናል፡፡

፳፩. በገቢ ስለመጠቀም

፩ ሆስፒታሎች /ጤና ጣቢያዎች የሚያገኙት ገቢ በጤና ተቋሙ ስም በተከፈተ ልዩ የባንክ ሂሣብ ውስጥ ተለይቶ ይቀመጣል፡፡
፪ ሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች ከሚሰጡት አገልግሎት የሚያገኙት ገቢ ሙሉ በሙሉ ከበጀታቸው ተጨማሪ ሆኖ ለሥራዎቻቸው ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡
፫ የሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት አካል ኦዲት ይደረጋል ፡፡
፬ የሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀምን ዝርዝር አፈፃፀም የሚያሳይ መመሪያ ቢሮው ከፋይናንስ ቢሮው ጋር በቅንጅት ያወጣል ፡፡

፳፪. የጤና አገልግሎት ክፍያ

፩ ለከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት ሊፈጸም የሚገባው ክፍያ ልክ በካቢኔው እየተወሰነ ሥራ ላይ ይውላል፡፡
፪ የጤና ቢሮው የጤና አገልግሎት ክፍያ ልክን ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት እንደአስፈላጊነቱ እንዲከናወን በማድረግ የውሣኔ ሃሣብ ለከተማው ካቢኔ ያቀርባል ፡፡
፫ የጤና ቢሮው ከሆስፒታሎች ወይም ከክፍለ ከተማው ጤና ዴስክ ከአስተያየት ጋር የሚቀርብለት የአገልግሎት ክፍያ ተመን ለከተማው ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል፡፡

፳፫. የዕቃና አገልግሎት ግገር

፩ ጤና ተቋሞች የዕቃና አገልግሎት ግዥ የሚፈጽሙት የከተማው አስተዳደር የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያን በመከተል ይሆናል፡፡
፪ በራሳቸው ሀብት አመራርና አስተዳደር ለሆስፒታሉ ብቃት ያለው አገልግሎት መስጠት ለሚችሉ ባለሀብቶች ሆስፒታሎች ሕክምና ነክ ያልሆነ አገልግሎቶች በውል መስጠት ይችላሉ፡፡
፫ ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶች በውሉ ለሶስተኛ ወገን የሚሰጡበት ሁኔታ በቢሮ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፳፬. የጤና መድን ዋስትና

፩ የከተማው አስተዳደር የጤና መድን ዋስትና ለማቋቋምና ለማስፋፋት የሚረዱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡
፪ የጤና መድን ዋስትና የሚከተሉትን የአደረጃጀት ዓይነት መሠረት በማድረግ ያቋቁማል፤
ሀ) የግል ድርጅቶች በሚያቋቁሙት የጤና መድን ዋስትና ፓሊሲ ፣

i) Other health services to be provided free of charge on reason of future decision

2. Health institution that provides exempted health services shall keep adequate record and report same to the Head of the Bureau.

## PART FIVE
## FINANCES OF HOSPITALS /HEALTH CENTERS UNDER THE CITY GOVERNMENT

**20.** Sources of finance of Hospital/health centers
1. Block budget appropriated by the Addis Ababa City Government;
2. Revenue from medical services the hospital /health center provide and
3. Aid in cash and in kind obtained by the hospital / health center from domestic sources and sources outside the country.

**21.** Revenue utilization
1. Revenue obtained by hospitals/health centers shall ber deposited in a special bank account opened in the name of the hospital /health center.
2. In addition to the block budget appropriated to them by the government, hospitals/health centers are authorized to use all revenue they obtain from services they provide.
3. The collection and utilization of revenue obtained by hospitals /health centers shall be audited by a body authorized by the government.
4. A directive for the detailed performance of the collection and utilization of revenue obtained by the hospitals/health centers shall be issued by the bureau in consultion with finance bureau.

**22.** Health Service fees
1. The city cabinet shall determine fees payble for health services provided by health institution under the Addis Ababa City Government
2. The health bureau management shall cause, as necessary, study for the revision of fees and submit its proposal to to the city cabinet as the case may be.
3. The bureau shall, togetherwith its recommendations, submit to and get approval from the city council on the proposals it receives from the hospitals or township health desks.

**23.** Procurement of goods and services
1. Hospitals shall procure goods and services in accordance with the government procurement deirectives.
2. Hospitals may outsource non-clinical services by contract to private and other institutions that can provide efficient services to the hospital with their won resources and management.
3. The condition in which non-ckubucak servuces may be outsourced to third parties shall b e determined by the directives to be issued dby the bureau.

**24.** Health insturance
1. The city government shall create conducive environment for the expanision and establishment of health insurance schemes.
2. The health insurance scheme may be established based on the following types of organizationl;
   (a) Private health insurance policy;

ለ) የተለያዩ የማኅበረሰብ ተቋማት የጤና መድን ሥርዓት እንዲዘረጉ በማድረግ፣

ሐ) አሠሪዎች ለሠራተኞቻቸው የጤና መድን ፓሊሲዎች በመግዛት ወይም በራሳቸው የመድን ሽፋን እንዲቋቁሙ በማድረግ፣

መ) መንግሥት ለሠራተኞች ማኀበራዊ የጤና መድን በማቋቋም፡፡

## ክፍል ስድስት
## የማኀበረሰብ ተሳትፎ

፳፭. የተሳትፎው ዓላማ

የማኀበረሰብ ተሳትፎ ዋንኛ ዓላማ ኅበረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ የመከላከል አገልግሎቶች ለማጠናከርና በጤና ተቋሞች የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት ጥራት ለማሻሻል ይሆናል፡፡

፳፮. በዕቅድ ዝግጅት መሳተፍ

የመከላከል ኘሮግራም ነጸፊዎችና የጤና ተቋሞች በዕቅድ ዝግጅት ሂደት እንዲሁም የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ በሚካሄድበት ጊዜ ሁሉ አመቺ በሆነ መንገድ የአገልግሎቱን ተጠቃሚዎች አስተያየት ማግኘት አለባቸው፡፡

## ክፍል ሰባት
## የመንግሥት የግሉ ዘርፍ ትብብርና የአስቸኳይ ጊዜ ጤና አገልግሎት

፳፯ . የሥራ ከባቢን ስለማሻሻል

፩ ቢሮው የግሉ ዘርፉ በጤናው ሴክተር የበለጠ ተሳታፊ የሚያደርገውን ወሳኝ የማትጊያ ስልቶች በመለየት ሃሣብ ያቀርባል፣ በተጨማሪም የአቻ ተጽዕኖን በመጠቀም የተሻለ ከባቢ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

፪ ቢሮው የሙያ ሥነ ምግባርን በማስፈን ረገድ ከግሉ ዘርፍ ጋር የቅንጅት የሚሠራበትን ስልት ይነድፋል ፡፡

፳፰. የምክክር መድረክ

ቢሮው ከግሉ ዘርፍ ጋር በፖሊሲ ፣ በቴክኒካዊ፣ በአሠራርና በቅንጅት ላይ ለመምከር ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የምክክር ጉባዔዎችን ያካሂዳል፡፡

፳፱. ድጋፍ ስለማድረግ

፩ ቢሮው የግሉ ዘርፍ የጤና ተቋማት እንዲስፋፉ እና የአገልግሎታቸው ጥራት እንዲሻሻል የቴክኒክ ዕገዛ ያደርጋል፡፡

፪ ቢሮው በመንግሥት የሚደረጉ የሥልጠናና የአሠራር መመሪያዎች ዝግጅት ላይ የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍ ያደርጋል፡፡

፴. መረጃን ስለማጠናከር

፩ የግሉ ዘርፍ የሚያደርገውን ተሳትፎና የሚያጋጥመውን ችግር በአግባቡ ማውቅና እርምጃ መውሰድ እንዲቻል ቢሮው በግሉ ዘርፍ ላይ ውቅታዊ የመረጃ ልውውጥ የሚኖርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ጥናቶች በቋሚነት ያካሂዳል፡፡

፪ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የጤና ተቋማት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ስለበሽታዎች ዓይነት እና ሥርጭት ወቅታዊ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ አለባቸው፡፡



(b)

(c) by encouraging communities to establish their won health insurance scheme;

(d) by encouraging employers to established their own health insurance schemes or to buy insurance policies;

(e) by establishing social health insurance schemes to civil servants.

## PART SIX
## COMMUNITY PARTICIPATION

**25.** Objective of Participation

The main objective of community participation is to strengthen the preventive and promotive care and to raise the quality of health services of health instituions.

**26.** Participation in Planning

Preventive health functionaries and health institutions may whenever possible get the views of the beneficiaris in the process of preparation of plans as well as during evaluation of implementation of such plans.

## PART SEVEN
## Public, Private Sector Cooperation and Emergency Health Service

**27.** Improving the working environment

1. The bureau shall indientify and proposes revisions on key incentives in addition use perr pressure among the private sector participants to promote their increased and active participation.
2. The bureau shall develop a strategy to work together with the private sector to ensure that health services are conducted in proper code of conduts.

**28.** Consulation forum

The burearu shall, at least twice a year, conduct a consultative forum with private sector on ploicyk, technical, systemic and coordination issues .

**29.** Support

1. The bureau shall give the necessary technical assistance to private health institutions with the objectives of enabling them to expand and improve quality of services.
2. The bureau shall case the participation of private sector in government, sponsored relevant trainings and development of guidelines.

**30.** Strengthening of informantion base

1. The bureau shall collect informantion on regular bases and undertake studies on the participation and constraoints of the sector to know and take actions to foster its participation.
2. Public and private health instiutions shall exchange information concerning type and spread of diseases in accordance with the directive to be issued by the bureau.

**፴፩ የአስቸኮይ ጊዜ የጤና አገልግሎት**

፩ ቢሮው በአገር አቀፍ በተለይም በከተማው ውስጥ በወረርሽኝ መልክ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ የበሽታ ዓይነቶችን በመለየት፣ ተገቢውን መረጃ ወቅታዊና ቀጣይ በሆነ መልኩ ያሰባስባል ያሰራጫል፡፡

፪ ቢሮው በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የጤና አገልግሎት የአመራር አካላትና የጤና ድርጅቶች አደጋ ከመድረሱ በፊት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የመረጃና የሎጂስቲክስ አቅም እንዲገነቡ እንዲሁም የመጠባበቂያ ግብዓችን እንዲመቻ ያደርጋል፡፡

፫ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋዎች የተነሳ የሚያደርሰውን የሕዝብ ጤናና ሕይወት አደጋ ለመቀነስ እንዲቻ ቢሮው የበኩሉን ተሳትፎና አስተዋጽኦ በተለይም የኅብረተሰቡን ንቁ ተሳትፎ በማስተባበር የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎትን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ያስፈጽማል፣ ክትትል ያደርጋል፡፡

**ክፍል ስምንት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

፴፪. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩ ካቢኔው ለዚህ አዋጅደ አፈጻጸም የሚያግዝ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪ ቢሮው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዱ ዝርዝር መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፴፫. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፴፬. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

ይህ አዋጅ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ሰኔ ፱ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር

**31.** Emergency Health Service

1. The bureau shall timely collect, analyze and distribute information on diseases that are likely to trun to epidemic proportions nationally and particularly in the city.
2. The bureau shall build the information, logistic capacity of health managers and institutions as well as prepare contingency stock of inputs to prevent eqidemic and to respohd as immediately as possible.
3. The bureau shall organize and implement the delivery of emergency health services with the full participation of communities in general and all stake holders in participation to reduce dealth and human sufferin; monitor the implementation of same.

PART EIGHT

MISCELLANEOUS PROVISIONS

**32.** POWER TO ISSUE REGULATION AND DIRECTIVES

1. The cabinet shall issue regulations for the proper implementation of this proclamation.
2. The Bureau shall issue detailed directive that will facilitate the implementation of this proclamation.

**33.** Inapplicable laws

Any proclamation, regulations, directive or practices, which are inconsistent with this proclamation, Shall have no application with respect to matters provided for in this proclamation.

**34.** Effective date

This proclamation shall come into force as, of the publication on the addis negari gazeta.

Done at Addis Ababa

This 17th day of June 2003,

Provisional Government of Addis Ababa City